*እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ*

## **ሕዋሶቻችንን በሥራ ማስለመድ** (getting our senses exercised by reason of use)

## መግቢያ

**ከተማርነውና ከተሰበክነው ነገር የተነሳ ለምንድን ነው ተለውጠን ያልቀረነው?**
**እያወቅንስ የምናጠፋው / የምንደክመው ለምንድን ነው?**
**እምናስበውን / እግዚአብሔር የሚያይልንን / ያንን ሰው የማንሆነው ለምንድን ነው?**

ዕብ 5: 11_14
ስለ እርሱም የምንናገረው ብዙ ነገር አለን፥ ጆሮቻችሁም ስለ ፈዘዙ በቃል ልንተረጕመው ጭንቅ ነው። ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፥ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም። ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለ ሆነ የጽድቅን ቃል አያውቅምና፤ ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በስራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው (have their **senses exercised by reason of use**) ለፍጹማን ሰዎች ነው።

1 ጢሞ 4: 7, 8
ነገር ግን ለዚህ ዓለም ከሚመችና የአሮጊቶችን ሴቶች ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ። እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ። ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና፤ እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው፥ ለነገር ሁሉ ይጠቅማል።

ምሳ 22:6
ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው (**train up a child**)፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።

**መልካም ልማድ**
በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።
ዕብ 10:25

**ክፉ ልማ ድ**
ምንዝር የሞላባቸው ኃጢአትንም የማይተዉ ዓይኖች አሉአቸው፤ የማይጸኑትን ነፍሳት ያታልላሉ፤ መመኘትን የለመደ ልብ አላቸው፤ የተረገሙ ናቸው።
2 ጴጥ 2:14

**የተሳሳተ / ያልተፈለገ ልማድ**
ኤፍሬም ማበራየት እንደ ለመደች ጊደር ነው፥ እኔ ግን በአንገቱ ውበት እጫንበታለሁ በኤፍሬም ላይ እጠምድበታለሁ፥ ይሁዳም ያርሳል፥ ያዕቆብም አፈሩን ያለሰልሳል።
ሆሴ 10:11

**"ምንም" ያለመልመድ**
ከከነዓናውያንም ጋር መዋጋት ያላወቁትን እስራኤልን በእነርሱ ይፈትናቸው ዘንድ፥ በፊትም ሰልፍን ያልለመዱ የእስራኤል ልጆች ትውልድ መዋጋትን ያውቁና ይማሩ ዘንድ እግዚአብሔር ያስቀራቸው አሕዛብ እነዚህ ናቸው
መሳ 3:1-2

## ምን ይሻላል?

**ምክንያት ማብዛቱን ትተን ራሳችንን ማስለመዱን እንቀጥል!**

**ለትምህርታችን ከታሪክ፥**
Liu Chi Kung, who placed second to Van Cliburn in the 1948 Tchaikovsky competition, was imprisoned a year later during the Cultural Revolution in China. During the entire seven years he was held, he was denied the use of a piano. Soon after his release, however, he was back on

tour. Critics wrote in astonishment that his musicianship was better than ever. “How did you do this?” a critic asked. “You had no chance to practice for seven years.”
“I did practice,” Liu replied, “every day. I rehearsed every piece I have ever played, note by note, in my mind.”

**ቃሉ! ?**
የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት <u>በጽድቅም ላለው ምክር</u> (<u>for training in righteousness</u>) ደግሞ ይጠቅማል።
2ጢሞ 3:16
--------------------------------------------------------

# ክፍል አንድ፡- ዓይን / እይታ

<u>1 *ራስን ማስለመድ ለምን*?</u>

## የምልልስ ሕይወት



